ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ
በ ሚያዚያ 21 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## እሪ በል ኤፍራታ ! ኡኡ በይ ማጀቴ !--መላይቱ ሀገሬ!

የዛሬ ሠላሳ ዐመት አካባቢ፤ በዘረኝነት መርዝ የተለከፉ ቡድኖች፤ በኢትዮጵያ ላይ የአጋንንት በረት ከፈቱ ። ዓላማቸው ፤ ሀገሪቱ በአጋንንት ተንኮል እርስ በእርሷ እየተተረማመሰች ሠላምና መረጋጋት እየናፈቃት በጦርነት ወስጥ እንድትኖር ነበር ። ከሞላ- ጎደልም ቢሆን ዕቅዳቸው አልተሳካላቸውም ማለት ግን አይቻልም ። ይኽን አባባል የወቅቱ ሁኔታ እየመሰከረው ያለ ሀቅ ነው። ግን ደግሞ ሌላ የማይታበል ሀቅ አለ። ይኸውም፤ ያ እነርሱ የከፈቱት የአጋንንት በረት ፤ እነርሱንም እያመሰና እያንኮታኮተ መሆኑ ነው ። ሠላም ሠላም የሚሉ ሁሉ፤ ለሠላም የሚበጅ ተግባር ስለአልሰሩ ፤ ሠላምን ሊያገኟት አልቻሉም ። ኢሕአዴግ በሥልጣን እስካለ ድረስ ፤ የሀገሪቱ የሠላም ምኞት የምድረ-በዳ ውልብልብሊት ሆኖ ይቀራል እንጅ፤ ሀገሪቱ ሠላም አይኖራትም ። ይኽም ሀቅ በታሪክ ተደጋግሞ የተረጋገጠ ነው ።

በተደጋጋሚ፤ ሀገራችንን ሠላም የነሷት ፀላኢ ሠናያት ሁሉ ወደ ማይቀርላቸው ከርሰ-መቃብር ወርደዋል። ወያኔም ወደ ከርሰ -መቃብሩ የተላከ መሆኑ ቢታወቅም፤ ገና አፈር አለበሰም ። የወያኔ ባለስልጣኖች በመቀሌ ከተማ ዋይታና ሀዘን በማሰማት ላይ ናቸው። ዋይታቸው የሀገሪቱን ሠላም ቢረብሸውም፤ ሌላው የትግራይ ሕዝብ ግን ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኖ ብሩኅ ተስፋን እየተጠባበቀ ይገኛል ። ኢትዮያዊነቱን ለድርድር የማያቀርበውን የትግራይ ሕዝብ፤ ከወያኔ ጋር ደምሮ ማየት፤ ሚዛነ- ቢስ -አመለካከት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፤ ሸማን እንደፈርጁ መልበስ ያውቅበታል ።

ያካባቢ ሀገራት ኢትዮጵያን ሠላም ነስተዋት ቆይተዋል ። ግብፅ፤ ሱዳን ፤ሊቢያ የመን፤ ሦሪያና ኢራቅ በግልም ሆነ በጋሪዮሽ፤ ሀገራችን ተከፋፍላና ተጨረማምታ እንድትቀር ሞከረዋል። የእነኝኽ ተጠቃሽ ሀገራት መሪዎች ግን እራሳቸውንም እንኳን፤ ሊያድኑ አልቻሉም። ባልቸገራቸውና በማያገባቸው የኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ ሀገራችንን ሠላም ሲያሳጧት የነበሩ ሁሉ በራሳቸው ተንኮል የራሳቸውን ሠላምና ፀጥታ እያጡ ወደ መቃብሮቻቸው ወርደዋል ። ሀገራችን ግን ፤ እየተውገረገረችም ቢሆን ፤ ህልውናዋን ይዛ ቀጥላለች !

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጠል የለባትም ብለው የተፍጨረጨሩ፤ ጠላቶቿን ሁሉ፤ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ብቅ እያሉ እንደ ጧት ጤዛ የከሰሙትን ሁሉ መዘርዘር አስፈላጊ አልሆነም ። የታሪክ ክስመት አክስሟቸዋልና የዛሬው ትውልድ ታሪክን እያገናዘበ ሀገሩን ከአደጋ የመጠበቅ ግዴታ እንዳለው ፤ ለማስታወስ ግን፤ ኃላፊነት አለብን ። ኢትዮጵያ ግን ዘለዓለማዊነቷን አስመስክራ እስካሁን ቀጥላለች ። እየቀጠለችም ፤መቀጠሏን ትቀጥላለች ። ቤኒቶ ሙሶሊኒ፤ የተሰኘው፤ የፋሽስት ኢጣሊያ መሪ፤ ወደ ኢትዮጵያ ያዘመተውን ወራሪ ጦር ሲሸኝ ባደረገው ዲስኩር፤ "**ሁሉንም ጨርሱና ብቻችሁን ተመለሱ !**" ብሎ ተናገረ ይባላል ።

የጣሊያን ወራሪ ወታደሮች በታዘዙት መሠረት የቻሉትን ያኽል ሕዝብ ቢፈጁም፤ በዐርበኞቹ አባቶቻችንና እናቶቻችን ቆራጥ ተጋድሎ ከሀገራችን ተባርረዋል። ሦስተኛ እንደማይመጡ ሆነው ተዋርደው ሄደዋል ! አሁን የመጡባት ጠላቶች ግን የውጭ ባዕዳን ሳይሆኑ ፤ ሀገር -በቀል ባላጋራዎች ናቸው ። በዘር ላይ የተመሰረተ የአጋንንት ሳጥን የከፈቱት ዘረኛ ድርጅቶች ፤ በሳጥኑ ውስጥ እየተንከባለሉ ይፍጨረጨራሉ ። ከዘር ሳጥን ለመውጣት አይፈልጉም ። በሳጥን እየኖሩ ፤ ጤናማ ዐየር ሊተነፍሱ ባለመቻላቸው ጤናቸው የተሟላ አልሆነም። ለዚህ ይመስላል ራሳቸው ጤና አጥተው ፤ የሕዝቡንም ጤና የሚነሱ !

ከአያሌ ዘመናት ዝግጅት በኋላ ዛሬ፤ እነኝህ ሀገር በቀል ነን ሊሉ የሚክጅሉ ድርጅቶች፤ ፤ የገዛ ሀገራቸውን ለማጥፋት ያጋንንትን በረት ከፍተው ፤ በዘር ፖለቲካ ሕዝቡን እርስ በርስ እንዲፋጅ ለማድረግ የሚጥሩት። ሀገሪቱንም የ 100 ዓመት የቤት ሥራ እንሰጣታለን ያሉትን ምኞት በመተግበር ላይ ናቸው ። የሀገሪቱ ጠንካራ አምድ ከነበሩት መካከል ሁለቱን ማለትም፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያንና የአማራ ተወላጆችን ለማውደም፤ ጠንክረው እየሰሩ እንደሆነ የአደባባይ ምሥጥር ከሆነ ቆይቷል ።

**ሰሞኑን በሸዋ ክፍለ-ሀገር በኢፍራታና አካባቢዋ የሚኖሩትን ሠላማዊ ዜጎች በግፍ ጨርሰዋቸዋል ።** ሕጻናት-ነፍሰ ጡሮችና አረጋውያኑ ያለ ርህራኄ በከባድ መሳሪያ ተጨፍጭፈዋል ። ሁሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተክርስቲያን አማኞች ናቸው። የሞቱትንና የቆሰሉትን ሠላማዊ ነዋሪዎች ቁጥር በትክክል ማወቅ አልተቻለም።ይኽንን የጭካኔ ድርጊት የፈጸሙት በብሄር ተደራጅተው ፤ የቡድንና የነፈስ-ወከፍ ከባድ መሳሪያ የታጠቁ ዘረኞች እንደሆኑ የዐይን ምስክሮች አደባባይ በመውጣት እንባ እየተናነቃቸው መስክረዋል ።

ኢትዮጵያ ሀገረ-ዕምነት ነች ። ሦስቱም ታላላቅ ሃይማኖቶች ፤ 1. አሪታውያን ፤ 2. ክርስቲያኖችና 3.ሙስሊሞች፤ ከአንድ መሠረት የወጡ ናቸው። ሁሉም፤ የአብርሀምን አምላክ ያመልካሉ ። ፀሎታቸውንም የሚጀምሩት " አምላከ-አብርሐም " በማለት ነው። መሠረታቸው አንድ በመሆኑም ፤የጋሪዮሽ ሃይማኖቶቻቸውን በጋራ ሀገራቸው ተስማምተው እያመለኩ ይኖራሉ። በየግል ዕምነታቸው ጣልቃ ሊገባባቸው የሚሻውንም ሁሉ ፤ በጋራ ሲከላከሉት ቆይተዋል ። ይኽም ዕውነታ፤ ኢትዮጵያን ያማኞች ሀገር ተብላ እንድትጠራ አድርጓታል ።

ዕምነታቸውን በነፃ ለማምለክ ባለመቻላቸው ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱትን ባዕድንንም ፤ አገሪቱ የፍቅር እጆቿን ዘርግታ በሠላም እንዲኖሩ አድርጋለች ። ኢትዮጵያ " **እጆቿውን ወደ እግዚአብሄር እየዘረጋች "** መኖሯ ብቻ ሳይሆን፤ የዕምነት ነፃነታቸውን ለተገፈፉት ባዕዳን ሰደተኞች ጭምር ፤ የፍቅር እጆቿን እየዘረጋች የምትቀበል ሀገር ነበረች። አሁን አሁን ፤ ያ ሁሉ ቀርቶ ፤ ዛሬ የራሷ ዜጎች ፤ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ተሰድደዋል። የዚህ ዋና ምክንያቱ በተወለዱበት፤ ባደጉበትና አባት እናት፤ አያት ቅድመ አያቶቻቸውና ዘመድ አዝማዶቻቸው፤ ኖረው ባለፉባት ሀገራቸው በሠላም ለመኖር ባለመቻላቸው ነው።

ባለፈው ሣምንት ፤ በሰሜን ሸዋ የሚኖሩትን የኦርቶዶክስ ተዋኅዶ እምነት ተከታዮችን በረቀቀ ተንኮል፤ ኢሕአዴጋዊ የብሄር ነፍጠኞች ፤በጭካኔ አጥፍተዋቸዋል ። ለቆሰሉቱ ጉዳተኞችም አስቸኳይ የህክምና ርዳታ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ብዙዎቹ ህይወታቸው ሊተርፍ አልቻለም ። አገዛዙ ሊያድናቸው ይቅርና ጩኸታቸውን እንኳ ለመስማት አልሞከረም። ይኽ ሀቅ የሚያረጋግጠው ፤ ሥልጣን ላይ የተቀመጠው ቡድን የጠባቦቹ ወንጀል ጠንሳሽም ተካፋይ ፤ መሆኑን ነው ። የተጠቂዎቹን ዋይታና ለቅሶ ሰምቶ የተጠቂዎቹን እምባ የሚያብስ ኃይል አልተገኘም ። በሀገሪቱ ውስጥ በርካታ መንግሥታት ስለሚተረማመሱ፤ ተጠያቂው ማን ሊሆን እንደሚችል፤ ሁሉም ግራ ተጋብቷል።

የኢፍራታ፤ ግደም፤ ዔፌሶን፤ ማጀቴ ፤ ከሚሴ እና ቆሬ ሜዳ አሰቃቂ ጥቃት ተፈጽሞበታል ። በቆሬ ሜዳ ያለው የአቡነ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል ። ነዋየ ቅዱሳን፤ ቅርሣ- ቅርሶችና አልባሳት ተመዝበረዋል ። ይኽንን ሁሉ ድርጊት የፈፀመውና ያስፈጸመው የኦነግ ጣታቂ ኃይል እንደሆነ ጥቃቱ የተፈፀመባቸው ነዋሪዎች የሃዘን እምባ እየተናነቃቸው ተናግረዋል ። ጅግናው የሰሜን ሸዋ ክፍለ ሀገር ሕዝብ፤ ወራሪው የኢጣሊያን ፋሽስት ጦር እንደፈፀመበት በደል ዓይነት ግፍ ደርሶበታል ። ውርደትንና ጥቃትን እንደ ሞት የሚቆጥረው ፤ ያ ጀግና ሕዝብ ፤ በገዛ ወገኖቹ በኦነግ ታጣቂዎች ተጠቅቷል ። ተገድሏል።

ታርሰም ተሸምቶም ተከፍቶም ተገፍቶም፤<br>
ተባርሮም ተስዶም፤ ለምኖም ተዋርዶም፤<br>
ይበላል እንጀራ ፤<br>
ጥቃት ነው አዋራጅ የሞት ባልንጀራ !<br>
እያለ ያንጎራጉራል ዛሬ የሰሜን ሸዋ ሕዝብ !

ዛሬ ይኽ አሰቃቂ ጥፋት የደረሰበት የሰሜን ሸዋ አካባቢ ነዋሪ ፤ በኢጣሊያ ወረራ ዘመን እንኳ ፤ የጠላት ጦር ሊደፍረው እንዳልቻለ ታሪክ መዝግቦለታል። በርካታ ስመጥር ዐርበኞችን ያፈራ የኢትዮጵያ እምብርት ነበር ። ለአብነት ያኽል ጥቂቶቹን መዝግቦ ማለፍ ያስፈልጋል ። ኃይለ ማርያም ማሞ፤ አበበ አረጋይ ፤ መስፍን ስለሺ ፤ ተሰማ ዕርገጤ እና ሌሎቹም የበቀሉበት አከባቢ ነበር ። ብዙ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ፤ ደራሲያን ፤ የኃይማኖት አባቶችና መሪዎች ፤ መነኮሳት ፤ የቅኔ- የዜማ ፤ የትርጉም ፤ የዝማሬና የፍልስፍና ተመራማሪዎችን ያፈራ ክፍለ ሀገር ነበር ።<br>
ሰሜን ሸዋ ፤ አያሌ ስመ-ጥር የሀገር መሪዎችንም አፍርቷል ።

ተተኪው ትውልድ፤ የእነኝህ ሰማዕታት ወላጆች አፅም ፤ እሾከ ሆኖ እንዳይወጋው ፤ አንድ ቁም ነገር መስራት ይጠበቅበታል ። ዘረኞች የሚፈፅሙበትን የግፍ -ግፍ ታግሎ በማስወገድ፤ ሀገሩንና ራሱን ነፃ ማውጣት አለበት ! እራሱን

በራሱ ነፃ ያላወጣ ትውልድ፤ ለሚቀጥለውም የባርነት ዘመን እራሱን እያዘጋጀ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል ። ከኢሕዴግ አጋዛዝ ፤ የነፃናት ምፅዋዕት ሊጠብቅ አይገባውም። ነፃነት የሚገኘው ፤ ከቀማኞች እየተነጠቀ እንጅ በምጽዋት አይደለም ። በመሥዋ ዕትነት የሚገኝ ነፃነት ሁሉ ዋስትና ሊያገኝ የሚችለው ግን ሕዝብ፤ በዴሞክራሲ ሥር ዓት፤ የህግ የበላይነትን አረጋግጦ ራሱን ማስተዳደር ሲችል ብቻ ነው ። በመሆኑም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ዘረኛውን አገዛዝ ካስወገደም በኋላ፤ የዴሞክራሲ ሥር ዓትን ለመገንባት ከባድ ተግባር እንድሚጠብቀው ያውቃል ። የሽግግር ሂደት ያለውም ለዚህ ነው ። የአሁን ቀዳሚ ተግባር ግን ሀገሩን ከጥፋት ማዳን ፤ የቅድሚያ ቅድሚያ መሆኑን ተረድቶ ፤ ትኩረቱም፤ ጥረቱም፤ አቅሙም ፤ ርብርቡም ሆነ ዐላማው እንደሆነም ተገንዝቧል።

ለወያኔ -ኢሕአዴግ፤ ኢትዮጵያን ማጥፋት ማለት፤ መሬቷን መቆራረስ፤ ህዝቧን መከፋፈል፤ ዳር ድምበሯን ማስደፈር ፤ ትውልድን ማፈናቀል፤ ሀብት-ንብረት መዝረፍ፤ ብቻ አይደለም ። የኢትዮጵያን የቆየ ታሪክና ቅርስ፤ ባኅልንና ወግን፤ ሥነ ምግባርንና ዕሴትን፤ ሃይማኖታዊ ተቋማትን ሁሉ እንዳልነበሩ አድርጎ ማፋለስና ማውደምንም ሁሉ የሚያጠቃልል ስትራተጂያዊ ዘላቂ ዕይታም ጭምር ማለት ነው ። ሀገርን ማጥፋት ማለት፤ ቤት ማቃጠል፤ ሀብት ንብረት መዝረፍ ሕዝብ -ትውልድ መምተር ፤ ቤተሰብ ማፍለስም ብቻ አይደለም ። ኢትዮጵያዊ ሥነልቦናን ፤ እንዳልነበረ አድርጎ ማውደምም ጭምር ነው ። ፍርሃትን ፤ አንገት መድፋትን ፤ ተሸቆጥቁጦ መገዛትን፤ አዲሱ ትውልድ በርካሽና አልባሌ ባኅል እንዲዘፈቅ ማድረግንም ሁሉ ያጠቃልላል። የሁሉም ጥፋቶች ማጠቃልያ፤ የሃይማኖት ተቋማትንና የዕምነቱን ተከታዮች ማጥፋትና እነዳያንሰራሩም ማድረግ ነው ። ሰሞኑን በሰሜን ሸዋ የተፈፀመው አሰቃቂ- ወንጀል፤ በጌዴዎ፤ ቡራዩ፤ ለገጣፎ፤ ደምቢዶሎ ፤ወዘተ የተፈጸመው-- ወንጀል ሁሉ ፤ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከሚካሄደው ዕቅድ ጋር የተያያዘም ጭምር መሆኑን መረዳት ይገባል ።

" ፍየል በግርግር " እንደተባለው እየሆነ የመጣ ሁኔታ ይታያልና ፤ ጥቃቅን አዕምሮ ያላቸው ቡድኖች ፤ ሀገራቸውን ደፍረው አስደፍረዋታል። ሀገርን መድፈር ፤ ሀፍረት እንጅ ጀግንነት አይደለም ። ሀፍረተ-ቢሶች ፤ የሀፍረት ነጠላ ስለሚከናነቡ ፤ ፍርሃታቸውን ለመደበቅ ይመቻቸዋል ። ጀግና ግን ፤ ሕዝቡን አይንቅም ። ያከብራል እንጅ ! ጀግና ትውልድ፤ ወገኑን ይወዳል ያፈቅራል ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ይሰዋለታል እንጅ፤ አዋርዶ ለአዋራጅ አይሰጠውም ።

በውስጥም ሆነ ከሀገሩ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንገቱን አቅንቶ ኮርቶና ተከብሮ መኖር ከፈለገ ፤ መጀመሪያ የሀገሩን ሉዕዋላዊነትና የሕዝቧንም አንድነት ጠብቆና አክብሮ መገኘት አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወነውን የሕዝብ ጥቃትና ውርደት ማስቆም አለበት ። ሊቆም የሚችለውም በመንግሥት ዐዋጅና ነጋሪት ጋዜጣ አይደለም ። በሕዝብ አመፅ በሚመጣ ዴሞክራሲያዊ ሥር ዓት ብቻ እንጅ ። የሥር ዓት ለውጥ መምጣት አለበት ብሎ የሚፈልግ ሁሉ፤ ፍላጎቱ እውን እንዲሆን ፤ ለተግባራዊነቱ ቆርጦ መነሳት አለበት ። ሌላ፤ ወለም-ዘለም የሚባል ፈሊጥ የለም። ቆርጦ የተነሳ ሕዝባዊ ወገን ፤ ሁለት ምርጫዎች አሉት። አንደኛው ሁሉም ቆርጦ በመነሳት፤ ራሱን ከውርደት፤ ሀገርንም ከጥፋት ማዳን የዜግነት ግዴታው መሆኑን ማወቅ አለበት። ቋሚ-ዘለቄታ መፍትሄውም ሀገርን ማዳን እንጂ ሌላ ሊሆን

አይችልም። የመፍትሄውም ቁልፍ የሥርዓት ለውጥ ብቻ ነው። የሥርዓት ለውጥና መሠረታዊ ለውጥ ተለያይተው የሚታዩ አይሆኑም ።

አሁን የሚታየው በውሽልሽል የታጀበ የጥግንግንና የይስሙላ ለውጥ ነው ። አጥፊና ጠፊ ፤ የተፋጠጡበት ፤ ዘራፊ የሚሸሽበት፤ ወንጀለኞች ያደፈጡበት ፤ ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚኬድ፤ ቢደቁም ራሳቸውን ያጋለጡበት፤ ያካሄዱ ቅደም-ተከተል የተዘበራረቀበት፤ በአዲስ ስልቻ አሮጌ ማር ለመከተት የሚግደረደርበት፤ ነው። የኃይል ሚዛኑ የተዛባበት ብቻም ሳይሆን፤ አሰላለፉም ቅጥ ያጣበት፤ የተሰፋው ጭላንጭል የደበዘዘበት መሆኑን ሕዝቡ ከተረዳው ቆይቷል ። በማር የተለወሰ ፕሮፓጋንዳ ማስማትን ተፈራራቂ መሪዎች ሞከረው ሞከረው ሕዝቡን ሊያታልሉት አልቻሉም። "የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን " የተባለውን ድለላ ሰምቶ ካሳለፈ በኋላ ፤ ጠርሙስ ሰባሪ መጥቶ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚል ፈሪና ፈርጣጭ ተተክቶ በሚያሳፍር ሁኔታ ሀገርን ለከሃዲዎች አስረክቦ መሸሹን ሕዝባችን ታዝቧል። ወያኔም ማንነቱ ድብቅ አልነበረም ። ፈሪዎች ጭካኔን ያበዛሉ። በጭካኔያቸው ሕዝቡን ጨርሰው በመጨረሻ አልሆን ሲላቸው ሕዝቡን ለሌላ ጨካኝ አስረክበው ይሸሻሉ። በአሁኑ ወቅት በየቦታው ውር ውር የሚሉት ዘረኞችም በበኩላቸው ፤ በብሄር ነፃነት ስም የትጥቅ ማስፈታት ፕሮፓጋንዳ ተጠቅመው ምን ያህል ጥፋት እንዳስከተሉ ታሪክ መዝግቦታል።

በአሁኑም ሰዓት፤ ወሃ ያልነካው ፤ ነፋስ ያልዳሰሰው፤ ፀሀይ ያልሞቀው የማር-ቅብ ፕሮፓጋንዳ እየተሰማ ነው ። ሁሉም ሲደመር " ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት " ከሚል ተረት አላለፈም ። አሁን ሥልጣን የጨበጠው ቡድን የድብብቆሽ ጨዋታ ተጋልጧል ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚጠይቀው መሠረታዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ለጥቂት ሰኮንድም አስቦት አያውቅም ። ኢትዮጵያዊ ይዘትና ዕቅድም-ተከተል የለውም ።

የወቅቱ ባለስልጣኖች የህዝቡን ማንነትና መስተጋብር በቅጡ ካለመረዳታቸው የተነሳ ፤ የለብ ለብ ፖለቲካን፤ በውቂው-ደብልቂው አካሄድ ለማስተናገድ እየሞከሩ እንደሆነ በግልፅ ይታያል ። መደመር የሚባለው ፈሊጥ፤ ለሂሳብ አስተምህሮ እንጅ ለፖለቲካው ጉልጓሎ የቱንም ያህል እንደማይፈይድ የብዙዎቹ መነጋገሪያ ሆኖ ቀርቷል። ይኽ አካሄድ ለማንም ለምንም አይጠቅምም። ለሀገርና ህዝብ ዘላቂ ጥቅም ከታሰበ የሚከተሉት ዐብይ ተግባራት መካሄድ አለባቸው ብሎ ሕዝቡ ያምናል። ይጠይቃልም።.

1ኛ. አሁን በሕዝብ ጫንቃ ላይ የወደቀው ህገመንግሥት ታግዶ ፤ ፓርላማውም ሊበተን ይገባል ።

**2ኛ** ሁሉንም ክፍሎች ያሳተፈ የሽግግር ሂደት መጀመር አለበት፡፡ ሀገሪቱን በጊዚያዊነት የሚያስተዳድር አካል ተግባሩ፤ ተልዕኮውና በሥልጣን የሚቆይበት ዘመን በአብዛኛው ስምምነትና በሕዝብ ይሁንታ ተወስኖ ወደ ሥራ መግባት አለበት።

**3ኛ.** በዘላቂነት ዴሞክራሲያዊ ሥር ዓትን ሊያሰፍን የሚያስችል፤ የዴሞክራሲዊ መድረክ ነፃ ሆኖ መንቀሳቀስ አለበት።

**4ኛ** የሀገሪቱን ዳር ድምበር፤ ሉዓላዊነት፤ የሕዝቡን ሠላምና ደኅንነት የሚጠብቅ የመከላከያ ሠራዊት ፤ የፖሊስና የፀጥታ አካላት በጊዜያዊ የሽግግር ተቋም ስር ሆነው ግዳጃቸውን ያከናውናሉ።

**5ኛ.** በሙያው የተካኑ ምሁራንን ያካተተና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሕዝብ የተመረጡ ወኪሎችን ያቀፈ የህገ መንግሥት አርቃቂ ጉባዔ ተመስርቶ ተግባሩን እንዲያከናውን ይደረጋል። ረቂቁ ሕገመንግሥት ለሕዝቡ ቀርቦ በመላው ሕዝብ ይሁንታን በማግኘት በሕዝብ ድምጽ ይጽድቃል ።
**6ኛ.** ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በነፃ ተወዳድረው አብላጫ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ፤ በረቀቀው ሕገ መንግሥት ውሳኔ መሠረት ሀገርን የማስተዳደር ኃላፊነት ይረከባል ።
**7ኛ.** ካንድ እስከ ስድስት ተራ ቁጥሮች የተመዘገቡት ተግባራት ፤ በሽግግሩ ወቅት የሚከናወኑ ሆነው፤ የሽግግሩ ሂደት ሥራውን ፈፅሞ ይሰናበታል።

ከላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ጉዳዮች ሳይከናወኑ አሁን ኢሕአዴግ ነገ ምርጫ ይደረጋል የሚለው ቀልድ፤ የልጆች ጨዋታ ከመሆን ያለፈ ርባና የለውም ። ሙጃውንና አረሙን ሳያስወግዱ፤ ዘር እንደመዝራት ይቆጠራል። " "አለባብሰው ቢያርሱ፤ በአረም ይመለሱ " ከመሆን ያለፈ ፋይዳ አያስገኝም። አካሄዱም ሀገሪቱን እንደገና ወደ አላስፈላጊ አዙሪት፤ቀውስና ደም መፋሰስ የሚከታት ነው የሚሆነው። የዙሪያ ጥምጥም ፖለቲካ እስካሁን ድረስ የተኬደበት ጉዞ ነበር። አላዋጣም። ስህተት ነበር ። ከስህተት የማይማር ኅብረተሰብ ደግሞ፤ ራሱን እየረገመ ከመኖር በቀር ፤ መፍትሄን አያመጣም ። የጥንት መሪዎች የጦርነትም ሆነ የሠላም ጥሪ ሲያስተላልፉ፤ **" አዋጅ! አዋጅ ! ስማ! ስማ ! ካልሰማህ ፤መስማሚያ ይንሳህ !" ይሉ ነበር ይባላል። ዛሬ ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ :" ልብ ያለው ልብ ይበል! ልብ የሌለው ልብ ይግዛ ! " እያለ እርስ በርሱ እየተጠራራ ይገኛል ።**

ይኸ ሕዝብ ፤ ያጋንንት በረት የከፈቱበትን አሰናብቶ ፤ በሠላምና በአንድነት የነፃነት ኑሮውን የሚመራበትን ዕድል ራሱ ይወስናል።በየጊዜው ሳይፈልጋቸውና ሳይጠራቸው እየመጡ፤ እኛ ብቻ እናውቅልሃለን ከሚሉ አምባገነኖች ይገላገላል። ይኸ ደግሞ ምኞት ሳይሆን ፤ ባልተቋረጠ የትግል አመፅ የሚመጣ ነው ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓም ትኖራለች !